Athletics Integrity Unit

ከ 20 ዓመት በታች የስፖርት ስነ-ምግባር መመሪያ

ይህ የስነ-ምግባር መመሪያ ለሁሉም አትሌቶች እና ለአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት አስፈላጊ የሆኑ የስፖርት ስነ-ምግባር እና ንጽህና መረጃዎችን በአንድ ላይ አጠቃሎ የያዘ ነው።

አትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት(AIU) ምንድን ነው?

የአትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት በዓለም አትሌቲክስ የተቋቋመ ገለልተኛ አካል ሲሆን፣ ለአትሌቲክስ ስፖርት ከዶፒንግ ጋር የተያያዙ እና ከዶፒንግ ውጪ ያሉ ሁሉንም የስነ-ምግባር ጉዳዮች የሚያስተዳድር ነው።

እኛ...

እናሳትፋለን
እንደግፋለን
እናበቃለን

እንሞግታለን
እናስተምራለን
መረጃ እናደርሳለን

እንመረምራለን
እናጣራለን
እንከሳለን

የአትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት (AIU) የሚከተሉትን ጨምሮልዩ ልዩ የስነ-ምግባር ጉዳዮችን የሚያስተዳድር ነው፡-

- ፀረ-ዶፒንግ
- የእድሜ ማጭበርበር
- የውድድር ማጭበርበር
- የውርርድ ህጎች መጣስ
- የዜግነት ለውጥ
- ደህንነቱ የተጠበቀ ስፖርት
- ጉቦ እና ሙስና

ዶፒንግ ምንድን ነው?

ዶፒንግ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ብቻ አይደለም። ዶፒንግ ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የፀረ-ዶፒንግ ሕግ መጣሶች መከሰት ነው።

ከሚከተሉት 11 የፀረ-ዶፒንግ ሕግ ጥሰቶች ውስጥ ሁሉም 11ዱ በአትሌቶች ላይ የሚተገበሩ ሲሆን፣ 7ቱ ደግሞ በአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ የሚተገበሩ ናቸው።

1. በአትሌት ምርመራ ናሙና ውስጥ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች፣ የንጥረ ነገሮቹ ተዋፅኦዎች ወይም ምልክቶች መገኘት
2. አትሌት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዘዴዎችን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር
3. አትሌቱ የምርመራ ናሙና ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ መሸሽ ወይም አለመስጠት
4. አትሌቱ የመገኛ አድራሻ መረጃ አለመሙላት እና/ወይም ለምርመራ ሳይገኝ መቅረት
5. በአትሌት ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው የዶፒንግ ቁጥጥር ሂደቱን ማወክ ወይም ለማበላሸት መሞከር
6. በአትሌት ወይም በአትሌቱ ድጋፍ ሰጪ አካላት (አሰልጣኝ፣ ሐኪም...) እጅ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ወይም ዘዴዎች ይዞ መገኘት
7. በአትሌት ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዘዴዎችን ማዘዋወር (ማከፋፈል) ወይም ለማዘዋወር መሞከር
8. ለአትሌት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዘዴዎችን መስጠት ወይም ለመስጠት መሞከር
9. .በአትሌት ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው በዶፒንግ ህግ ጥሰት ላይ ተሳታፊ/ተባባሪ መሆን ወይም ለመሆን መሞከር
10. አትሌቱ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው እገዳ ከተጣለባቸው የድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር የተከለከለ ግንኙነት ማድረግ
11. ጥሰቶችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዳይጠቁሙ ማደናቀፍ ወይም ጥቆማ ባቀረቡ አካላት ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ

የተከለከሉ ንጥረ-ነገሮች ዝርዝር

የዓለም አቀፍ የፀረ-ዶፒንግ ኤጀንሲ (WADA) የተከለከሉ ንጥረ-ነገሮች ዝርዝር በውድድር ወቅትም ሆነ በየትኛውም ጊዜ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን እና ዘዴዎችን ለይቶ ያብራራል። ይህ ዝርዝር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሻሻል ሲሆን፣ በየዓመቱ ከፈረንጆች ጥር 1 ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አትሌቶች የትኞቹ ንጥረ ነገሮች እና ዘዴዎች የተከለከሉ እንደሆኑ የማወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

እንዲሁም ሰውነታቸው ውስጥ ለሚገኝ ማንኛውም የተከለከለ ንጥረ ነገር፣ አስበውበት ያድርጉት ባለማወቅ፣ በግላቸው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ።

→ [የተከለከሉ ንጥረ -ነገሮችን ዝርዝር እዚህ ይመልከቱ]

ይህን ማወቅ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

መድኃኒቶችን ሲጠቀሙ ጥንቃቄ ያድርጉ

1. የዓለም አቀፍ የፀረ-ዶፒንግ ኤጀንሲን (WADA) ህግጋት መከተል እንደሚኖርብዎት ለሐኪምዎ ያሳውቁ።
2. በመድኃኒትዎ ውስጥ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን ያረጋግጡ

→ በ Global DRO አማካኝነት

3. የሕክምና ፈቃድ (TUE) ለእርስዎ የሚመለከት መሆኑን ያረጋግጡ፤ ከተፈቀደልዎትም ጥያቄዎን በተቻለ ፍጥነት ያስገቡ።

ድጋፍ ሰጪ ምግቦች (Supplements) ሲጠቀሙ በጣም ጥንቃቄ ያድርጉ

1. ድጋፍ ሰጪ ምግቦችን ከአስተማማኝና ከታመነ አቅራቢ ይምረጡ።
2. ድጋፍ ሰጪ ምግቦቹ የተረጋገጡ (certified) እና የምርት ስብስባቸው የተመረመረ (batch-tested) መሆኑን ያረጋግጡ

→ ለምሳሌ፡ በ Informed Sport፣ HASTA ወይም NSF የተረጋገጡ

- የሚወስዷቸውን አጠቃላይ መድኃኒቶች እና ድጋፍ ሰጪ ምግቦችን መዝግበው ይያዙ።
- በዶፒንግ ቁጥጥር ቅጽ (DCF) ላይ በግልጽ ያሳውቋቸው

የዕድሜ ማጭበርበር ምንድን ነው?

የዕድሜ ማጭበርበር የሚባለው፣ አንድ አትሌት የውድድር ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ሲል ዕድሜው ትልቅ ወይም ትንሽ ሆኖ እንዲታይ በሆነ መንገድ ዕድሜውን መቀየር ነው።

አትሌቶች፣ የስፖርት አመራሮች, ዳኞች እና የአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት ከዕድሜ ማጭበርበር ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው፤ ስለዚህ የእርስዎ ሥነ-ምግባር ትልቅ ዋጋ አለው።

የዕድሜ ማጭበርበርን ለመከላከል ምን ማድረግ ይችላሉ?

- ስለ ዕድሜዎ እና ስለተወለዱበት ቀን እውነተኛ ይሁኑ። የሐሰት ሰነዶችን ለማግኘት አይሞክሩ፣ ወይም ሌሎች በእርስዎ ስም እንዲያወጡ አይፍቀዱ።

- ፌዴሬሽኖች እና የአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ አትሌቶችን ለውድድር ሲመዘግቡ ወይም በኦፊሻላዊ የመረጃ ቋቶች (ለምሳሌ ለውድድሮች በሚዘጋጁ ዕውቅና ወረቀቶች/Accreditation) ላይ ሲያስገቡ የትውልድ ዘመናቸው ወይም ዕድሜያቸው በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ አለባቸው።

- ፌዴሬሽኖች እና የአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት የተመዘገቡ አትሌቶችን የመታወቂያ ሰነዶች ጥልቅ እና ዘወትር የሚደረግ ፍተሻ ማካሄድ እንዲሁም የመታወቂያው መረጃ ከዚህ ቀደም ከተያዘው መረጃ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

ማንኛውም ሰው የትውልድ ዘመንዎን ወይም ዕድሜዎን እንዲቀይሩ ቢጠይቅዎት፣ የጥፋቱ ተባባሪ ለመሆን እምቢ ይበሉ፤ እንዲሁም ድርጊቱን ለAIU ሪፖርት ያድርጉ። 🚨

የውድድር ማጭበርበር ምንድን ነው?

የውድድር ማጭበርበር:- የውድድሩን ውጤት ለመቆጣጠር ወይም የስፖርት ሁነቱን ተፈጥሯዊ ሂደት ለመቀየር የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ነው። ድርጊቱ የስፖርታዊ ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ሲባል፣ እና አንዳንድ በህገ-ወጥ የውርርድ ወይም የቁማር እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ሊፈጸም ይችላል።

የውድድር ማጭበርበር የውጤት መቀየርን፣ የስፖርት ማጭበርበርን፣ ሙስናን፣ ሆን ብሎ ዝቅተኛ አፈጻጸም ማሳየትን ወይም የውስጥ መረጃን ፈቃድ ለሌላቸው ግለሰቦች ማጋራትን ሊያካትት ይችላል።

ለአትሌቶች፣ የስፖርት አመራሮች እና የአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት የተደነገጉ ህጎች

- የውድድር ማጭበርበር ጥያቄ እንደቀረበልዎት ባወቁበት ቅጽበት ወዲያውኑ ሪፖርት ያድርጉ።
- በሚካሄዱ ማንኛቸውም ምርመራዎች ላይ ይተባበሩ።
- በአትሌቲክስ ስፖርት ውስጥ በሚካሄድ ማንኛውም ውድድር ላይ አይወራረዱ።
- የውስጥ መረጃን አያጋሩ።
  (እርስዎ ወይም በአትሌቲክሱ ውስጥ ያሉ ጥቂት ሰዎች የሚያውቁት፣ ነገር ግን ሰፊው ህዝብ የማያውቀው መረጃ)
- የውድድርን ውጤት ለመቀየር የሚደረግን ወይም ለእርስዎ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የሚሰጥን ማንኛውንም ነገር አይቀበሉ።
- ከውድድር ማጭበርበር ወይም ከማንኛውም ሌላ የሙስና አይነት ጋር የተያያዙ ጥቅሞችን አይስጡ፣ አይጠይቁ ወይም አይቀበሉ።

የዜግነት/ሀገር/ ቅያሪ (ዝውውር) ምንድን ነው?

አንድ አትሌት በዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮች ላይ የሚወክለውን ሀገር በይፋ በሚቀይርበት ጊዜ፣ ሂደቱ በዓለም አትሌቲክስ የተደነገገውን ጥብቅ ሥርዓት መከተል አለበት።

ከዚህ ሂደት ጋር ተያይዘው የሀገር ውክልና(የዜግነት) ዝውውር ጋር የተያያዙ ማጭበርበሮችን ሊያስከትሉ የሚችሉ በርካታ የታማኝነት/የስነ-ምግባር ስጋቶች አሉ፤ እነሱም፦ የሰነዶች ሀሰተኛነት፣ ያለጊዜው ሀገርን ወክሎ መወዳደር፣ ሊከሰት የሚችል የሰዎች ዝውውር፣ በኃይል ዶፒንግ ማስወሰድ፣ ሀሰተኛ ወይም ያልተፈጸሙ ቃላቶች፣ እና አትሌቶች ከዝውውር በኋላ ያላቸው መብቶች እና አጠቃላይ ደህንነታቸው መጎዳት ናቸው።

እነዚህን ስጋቶች ይወቁ፤ እንዲሁም ማንኛውንም ውሳኔ ከመስጠትዎ በፊት ህጎቹን ሙሉ በሙሉ መረዳትዎን ያረጋግጡ።

ደህንነቱ የተጠበቀ ስፖርት

የዓለምአትሌቲክስ የደህንነት ጥበቃ ህጎች በአትሌቲክስ ስፖርት ውስጥ ለሚሳተፉ ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ድጋፍ ሰጪ አካባቢን ለማረጋገጥ ለአትሌቶች እና ለአትሌት ድጋፍ ሰጪ አካላት ማዕቀፍ ያዘጋጃሉ።

ማንኛውም ሰው የሚከበርበትና ዋጋ የሚሰጠው ደህንነቱ የተጠበቀና ሳቢ አካባቢ መፍጠር የደህንነት ጥበቃ ዋና ዓላማነው።

በአትሌቲክስ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በስፖርቱ ውስጥ በዙሪያው ባሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸምን ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ብዝበዛ በንቃት የመከላከል ሀላፊነት አለበት።

ስለመብቶችዎ እና ሀላፊነቶችዎ ግንዛቤ መያዝ እርስዎን እና ሌሎችንም ደህንነታችሁን የጠበቀ ያደርጋል።

AIU
Integrity
Line

ማንኛውንም የህግ መጣስ ሪፖርት በማድረግ የድርሻዎን ይወጡ

መረጃዎችን AIU ጋር በማንኛውም ጊዜ በጥንቃቄና በሚስጥር ያጋሩ። ይህን በግልጽ ስም ሳይጠቅሱ ማድረግ ይቻላል፤ እርስዎ በራስዎ ፍላጎት ካልገለጹልን በቀር የርሶን ማንነት/የመገናኛ መረጃዎን አናይም።

WhatsApp

ከእኛ ጋር ማንነትዎን ሳይገልጹ ይገናኙ
የስልክ ቁጥርዎን፣ ስምዎን ወይም ምስልዎን ማየት አንችልም!

Email

ከፈለጉ ማንነትዎን ሳይገልጹ (ሚስጥራዊ እንደሆኑ) መቆየት ይችላሉ!

Web form

ደህንነቱ የተጠበቀውን የኦንላይን ቅጽ ያስገቡ/ይላኩ።
የእኛን ምላሾች ለማግኘት የመዳረሻ ቁልፍዎን (access key) ያስታውሱ ወይም የማሳወቂያ (notifications) አገልግሎቱን ይፍቀዱ።

"

የአሸናፊነት አስተሳሰብ እንዲኖርዎት «በማንኛውም ዋጋ ማሸነፍ አለብኝ» የሚል አስተሳሰብ አያስፈልግዎትም።

ኬቲ ሙን

የዓለም ሻምፒዮን እና የኦሊምፒክ ሻምፒዮን

ለእኛ ይጻፉልን

እርስዎን ለመደገፍ እዚህ እንገኛለን!

ማንኛው ምስጋት ወይም ጥያቄ ካለዎት፣
የአትሌቲክስ አቋም መከታተያ አካልን
AIU ለማነጋገር አያመንቱ።

education@athleticsintegrity.org

athleticsintegrity.org

aiu_athletics